Made with Xodo PDF Reader and Editor

Daniel Fikadu Law Office

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETTE
OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሠላሳ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፳፬
አዲስ አበባ የካቲት ፳፬ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

31st Year No. 24
ADDIS ABABA, 3rd March 2025

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፭፻፫፻፷፫/፪ሺ፲፯ ዓ.ም

የነዳጅ ውጤቶች ግብይት አዋጅ.....ገጽ ፲፯፻፹፮፻፹

CONTENT

Proclamation No.1363/2024

Petroleum Products Marketing Proclamation Page.....17680

አዋጅ ቁጥር ፭፻፫፻፷፫/፪ሺ፲፯
የነዳጅ ውጤቶችን የግብይት ሥርዓት ለመደንገግ የወጣ አዋጅ

ነዳጅ ውጤቶች ካላቸው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፋይዳ አንጻር ስትራቴጂክ ምርቶች በመሆናቸው አቅርቦታቸው፣ ክምችታቸው፣ ስርጭታቸው፣ ደህንነታቸው፣ ጥራታቸው እና ዋጋቸው ዓለም አቀፍ ደረጃዎችን በጠበቀ እና በሰውና በእንስሳት ጤና፣ በንብረትና በአካባቢ ላይ ጉዳት በማያደርስ ሁኔታ መከናወኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ፤

PROCLAMATION NO. 1363/2024
A PROCLAMATION ISSUED TO PROVIDE FOR THE MARKETING SYSTEM OF PETROLEUM PRODUCTS

WHEREAS, Petroleum Products are strategic for economic and social development and ensuring their supply, storage, distribution, safety, quality and price in compliance with accepted international safety and quality standards is essential to safeguard human and animal health, property and the environment;

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 1443.00

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹፻፩
Negarit G. P.O.Box 80001

Daniel Fikadu Law Office

CamScanner

Made with Xodo PDF Reader and Editor

ከአስመጪው ጀምሮ እስከ መጨረሻው ተጠቃሚ ድረስ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ፣ ቀልጣፋ፣ ግልጽ፣ አስተማማኝ፣ ፍትሀዊ እና ተደራሽ የአቅርቦት፣ የስርጭት እና የችርቻሮ የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት በነዳጅ ውጤቶች የግብይት ሰንሰለት ውስጥ እየታዩ ያሉ ሕገ-ወጥ ተግዳሮቶችን ለመቆጣጠር የሚያስችል ምቹ ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በዘርፉ የተሰማሩ የነዳጅ ተቋማትና ባለሙያዎች ዓለም አቀፍ ልምድ በሚጠይቀው መሠረት በሚፈለገው የብቃት ደረጃ ላይ የሚገኙ መሆናቸውን ማረጋገጥ ደህንነቱ የተጠበቀና ሕጋዊ የነዳጅ ውጤቶች የግብይት ሥርዓት ለማስፈን የላቀ ጠቀሜታ ያለው በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

ክፍል አንድ
ጠቅላላ ድንጋጌዎች

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የነዳጅ ውጤቶች ግብይት አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፷፫/፪ሺ፲፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

WHEREAS, it has become necessary to create a conducive environment to control illegal activities in the value chain of petroleum products from the importer to the end user by establishing a modern, effective, transparent, reliable, equitable and accessible supply,distribution and retailing transaction system;

WHEREAS,ensuring the required competence of institutions and professionals engaged in the sector in accordance with the prevailing international practice is essential to promote safe and legal marketing of petroleum products;

NOW THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

PART ONE
GENERAL PROVISIONS

1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Petroleum Products Marketing Proclamation No.1363/2024."

Daniel Fikadu Law Office

CamScanner

Made with Xodo PDF Reader and Editor

፪.ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/"የነዳጅ ውጤቶች" ማለት የተፈጥሮ ድፍድፍ ነዳጅን፣ ፔትሮሊየም ጋዝን፣ ባዮ-ፊውልን ወይም ሲንተቲክ ነዳጅን ከማጣራት ወይም ከማቀናበር የተገኘ ንፁህ ወይም አግባብ ባለው መንገድ የተደባለቀ የነዳጅ ውጤት ሆኖ ቤንዚንን፣ ኬሮሲንን፣ ናፍጣን፣ ቀላልና ከባድ ጥቁር ናፍጣን፣ የአውሮፕላን ነዳጅን፣የተሸከርካሪ ቅባትና ዘይቶችን ያካትታል፤

2. Definition

In this Proclamation, unless the context otherwise requires:

1/ "Petroleum Products" means organic compounds, pure or blended, which are derived from refining or processing of crude oil, bio-fuel or synthetic fuel and includes Benzene, Kerosene, Diesel, Light and Heavy Diesel oils, Jet fuel, Lubricans and base oils;

፪/"ባዮ-ፊውል" ማለት ከተፈጥሮ ነገሮች በባዮሎጂካል ሂደት የሚገኝ የታዳሽ ኃይል ምንጭ ነው፡፡

2/ "Bio-Fuel" means a type of renewable energy source derived from organic materials produced through biological process.

፫/"መደባለቅ" ማለት የተሻለ ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ ጠቀሜታ ለማግኘት የነዳጅ ውጤትን በህጋዊ መንገድ በተፈቀደለት ተቋምና በተቀመጠው የጥራት ደረጃ መሰረት ከባዮ-ፊውል ከተገኘ የነዳጅ ውጤት ጋር የማቀላቀል ተግባር ነው፤

3/"blending" means an activity of legally mixing petroleum products with Bio-Fuel products according to a legally approved facility and set quality standards to obtain better economic and environmental benefits;

፬/"ባዕድ ነገርን መቀላቀል" ማለት አለአግባብ ጥቅም ለማግኘት ሲባል በሕገወጥ መንገድ ዝቅተኛ ዋጋ ያለውን ነዳጅ ከሌላ የነዳጅ ውጤት ጋር ወይም የተቀመጠውን የጥራት ደረጃ ሊያጓድሉ ከሚችሉ ከሌሎች ነገሮች ጋር መቀላቀል ነው፤

4/"adulteration"means illegally mixing low-price petroleum products with other fuel products, or with other things that may compromise the set quality level in order to gain an unfair advantage ;

Daniel Fikadu Law Office

CamScanner

Made with Xodo PDF Reader and Editor

ሯ/"ማከማቸት" ማለት የነዳጅ ውጤቶችን የጥራት ደረጃቸውን ጠብቆ በቋሚ የነዳጅ ማጠራቀሚያ ዴፖ ማቆየት ነው፤

ሰ/ "ማንቀሳቀስ" ማለት የተለያዩ የማንቀሳቀሻ ዘዴዎችን በመጠቀም የነዳጅ ውጤቶችን ከኢትዮጵያ ውጭ ከሚገኝ የማከማቻ ተቋም ሀገር ውስጥ ወደሚገኝ የማከማቻ ዴፖ ወይም ሀገር ውስጥ ከሚገኝ የማከማቻ ዴፖ ወደ አከፋፋዮች፣ለመጨረሻ ተጠቃሚዎች ወደሚከፋፈሉበት ማደያዎች ወይም ወደ ቀጥታ ተጠቃሚዎች የማድረስ ሂደት ነው፤

ሸ/ "የነዳጅ ውጤቶች ግብይት" ማለት የነዳጅ ውጤቶችን ከውጪ ሀገር ከመግዛትና ማስመጣት ጀምሮ እስከ ችርቻሮ ንግድ ሥራ ድረስ ያለውን የእርስ በእርስ የንግድ ግንኙነት ያካትታል፡፡

ቀ/"የግብይት ሰንሰለት" ማለት የነዳጅ ውጤቶችን ከውጪ ሀገር ከመግዛትና ማስመጣት ጀምሮ እስከ ችርቻሮ ንግድ ሥራ ድረስ የሚሰማሩ የግብይት ተዋናዮችን የእርስ በእርስ መስተጋብርና ያላቸውን ግንኙነት የሚያካትት ትስስር ነው፤

በ/"የግብይት ተዋናይ" ማለት የነዳጅ ውጤቶችን ለማስመጣት፣ ለማደባለቅ፣ ለማንቀሳቀስ፣ ለማከማቸት፣ ለማከፋፈል፣ ለመችርቻቸር ወይም ተዛማጅ ተግባራትን ለማከናወን የንግድ ሥራ ፈቃድ

5/"Storage" means depositing petroleum products with their quality standard in a fixed storage depot;

6/"transporting" means delivering of petroleum products, using different means of transportation, from a depot facility located outside Ethiopia to a depot facility located in the country, or from a storage facility located in the country to distributers, fuel stations or direct users;

7/"Petroleum Products Marketing " means inter-business relations from buying and importing petroleum products from foreign countries up to gas station business.

8/"marketing chain" means the network comprising the relationship of market actors across the line from buying and importing petroleum products from abroad to retail business, and their interaction;

9/"market actor" means a person who is issued a business license to import, blend, transport, store, distribute or retail petroleum products or undertake other related, activities;

Daniel Fikadu Law Office

CamScanner

Made with Xodo PDF Reader and Editor

የተሰጠው ሰው ነው፤

፲/ "አስመጪ" ማለት የነዳጅ ውጤቶችን ከውጪ ሀገር ለማስመጣት የንግድ ሥራ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው፤

፲፩/ "አከፋፋይ" ማለት የነዳጅ ውጤቶችን ከአስመጪ ገዝቶ ለነዳጅ ማደያዎች ወይም ለቀጥታ ተጠቃሚዎች በጅምላ የሚሸጥ ሰው ነው፤

፲፪ "ነዳጅ ማደያ" ማለት የነዳጅ ውጤቶችን ከአከፋፋይ ገዝቶ ለመጨረሻ ተጠቃሚዎች በችርቻሮ የሚሸጥ ተቋም ነው፤

፲፫/"ቀጥታ ተጠቃሚ" ማለት የነዳጅ ውጤቶችን ከአከፋፋይ በጅምላ በመግዛት ለተፈቀደለት ፕሮጀክት ወይም የልማት ድርጅት ፍጆታ የሚያውል ሰው ነው፤

፲፬/"የመጨረሻ ተጠቃሚ" ማለት የነዳጅ ውጤቶችን በችርቻሮ በመግዛት ለራሱ ፍጆታ የሚያውል ሰው ነው፤

፲፭/"ዲጂታል የክፍያ ስርዓት" ማለት የነዳጅ ውጤቶች ሽያጭ እና ግዥን በኤሌክትሮኒክ ዘዴ መፈፀም ነው፤

፲፮/ "የፀና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት" ማለት የግብይት ተዋናይ የነዳጅ ውጤቶችን ለንግድ ወይም ለንግድ ላልሆነ ዓላማ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስመጣት፣

10/ "importer" means the person permitted to import petroleum products in accordance with the law;

11/ "distributer" means any person who buys petroleum products from an importer and sells in bulk to fuel stations or direct users;

12/ "Fuel Station" means any station that buys petroleum products from a distributer and sells in retail to the end users;

13/ "direct user" means a person who is granted a permit to buy petroleum products in bulk from a distributor and use them for the consumption of his approved project or government enterprise;

14/ "end user" means a person who buys petroleum products at retail and uses them for his own consumption;

15/ "digital payment system" means selling and buying petroleum products by electronic means;

16/ "valid certificate of competence" means a written evidence granted to a market actor witnessing his professional ability to import, blend,

Daniel Fikadu Law Office

CamScanner

Made with Xodo PDF Reader and Editor

ለመደባለቅ፣ ለማጓጓዝ፣ ለማከማቸት፣ ለማከፋፈል፣ ለመቸርቸር ወይም ተዛማጅ የሆኑ ተግባራትን ለማከናወን ሙያዊ ብቃት እንዳለው ለማረጋገጥ የሚሰጥ የጽሁፍ ማስረጃ ነው፤

transport, store, distribute or retail petroleum products or undertake such other similar activities for commercial or non-commercial purposes;

፲፯/ "የነዳጅ መሠረተ ልማት" ማለት የነዳጅ ውጤቶችን ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት፣ ለመደባለቅ፣ ለማጓጓዝ፣ ለማከማቸት፣ ለማከፋፈል፣ ለመቸርቸር ወይም ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ለማከናወን ጥቅም ላይ የሚውል ማንኛውም መሠረተ ልማት ነው፤

17/ "petroleum infrastructure" means any infrastructure used to import, blend, transport, store, distribute, retail or undertake such other related activities of petroleum products;

፲፰/"ግንባታ" ማለት የተያያዥ ህንጻዎችን ግንባታ ሳይጨምር የነዳጅ መሠረተ ልማት ግንባታ ነው፤

18/ "construction" means the construction of petroleum infrastructure, excluding the construction of related buildings;

፲፱/"ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር" ማለት አንደቅደም ተከተሉ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

19/ "Ministry or Minister " means the Ministry or Minister of Trade and Regional Integration respectively;

፳/"ባለሥልጣን" ማለት የነዳጅ እና ኢነርጂ ባለሥልጣን ነው፤

20/ "Authority" means the Petroleum and Energy Authority;

፳፩/"ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፯ መሠረት የተቋቋመ ማንኛውም ክልል ሲሆን ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ሲባል የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችንም ይጨምራል፤

21/ "Region" means any State referred in Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, and for the purpose of this Proclamation includes the Addis Ababa and Dire Dawa City Administrations;

Daniel Fikadu Law Office
CamScanner

Made with Xodo PDF Reader and Editor

፳፪/"አግባብ ያለው አካል" ማለት በክልል፣በአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች ንግድን ለማስተዳደር ሥልጣን የተሰጠው አካል ነው፣

፳፫/"ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፣

፳፬/ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ፆታ ይጨምራል።

22/ "Relevant Body" means an office authorized to administer trade in a Region , Addis Ababa and Dire Dawa City Administrations;

23/ "person" means any physical or juridical person;

24/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

፫. የተፈጻሚነት ወሰን

3. Scope of Application

፩/ይህ አዋጅ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚካሄድ የነዳጅ ውጤቶች ግብይት እና በግብይት ተዋናዮች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

1/ This Proclamation shall be applicable on the marketing and market actors of petroleum products in Ethiopia.

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም ይህ አዋጅ በሚከተሉት ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፦

2/ Notwithstanding the provision of sub-Article (1) of this Article, this Proclamation shall not be applicable:

ሀ) በነዳጅ ፍለጋና ልማት ዘርፍ በሚከናወኑ ሥራዎች እና

a) to petroleum exploration and development operations and

ለ) ለወታደራዊ አገልግሎት በሚውሉ የነዳጅ ውጤቶች አቅርቦት።

b) on the supply of petroleum products for military service.

ክፍል ሁለት

የግብይት ተዋናዮች ግዴታዎች

PART TWO

OBLIGATIONS OF MARKET ACTORS

፬. የአስመጪ ግዴታዎች

4. Obligations of an Importer

ማንኛውም አስመጪ የሚከተሉት ግዴታዎች

Any importer shall have the obligations

Daniel Fikadu Law Office

CamScanner

Made with Xodo PDF Reader and Editor

ይኖሩታል፡-

ፅ/የሀገሪቱን ፍላጎት መሠረት በማድረግ ዓመታዊ የነዳጅ ውጤቶች ግዥ ዕቅድ የማዘጋጀት፣ ከውጪ ሀገር የማስመጣት፣ የማከማቸት እና ለአከፋፋዮች የመሸጥ፣

ፆ/የሚያስመጣቸው የነዳጅ ውጤቶች ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውን ዓለም አቀፍ ነዳጅ ነክ ስምምነቶች እና የሀገሪቱን የጥራት ደረጃ መስፈርቶች ያሟሉ መሆናቸውን የማረጋገጥ፣

ፇ/ከመነሻ ወደብም ሆነ ከራሱ ዴፖዎች የነዳጅ ውጤቶችን ወደ ማጓጓዣ ለመጫን ጥያቄ ሲቀርብለት የሚጫነውን ነዳጅ ጥራት እና መጠን ትክክለኛነት አረጋግጦ ለአጓጓዡ የማጓጓዣ እና የጭነት ሰነድ የመስጠት፣

ፈ/ከመነሻ ወደብም ሆነ ከራሱ ዴፖዎች በየዕለቱ የሚጫኑትን የነዳጅ ውጤቶች አይነት፣ መጠን እና የተገዙበትን ዋጋ የሚያሳዩ መረጃዎችን የመያዝና ለባለሥልጣኑ ሪፖርት የማቅረብ፣

ፉ/ የዋጋ ቁጥጥር የሚደረግባቸውን የነዳጅ ውጤቶች አግባብነት ያለው የመንግሥት አካል በሚወስነው ዋጋ የመሸጥ፣

ፊ/ስላከናወናቸው ሥራዎች መረጃዎችን የመያዝ፣ የመተንተን እና በጽሑፍ ወይም በሚዘረጋ የቴክኖሎጂ የአሰራር

to:

1/prepare annual procurement plan of petroleum products based on the demand of the Country and import, store and sale same to distributors;

2/ ensure that imported petroleum products are in compliance with international petroleum agreements and the national quality standard requirements of the country;

3/ verify the quality and quantity of petroleum products to be loaded, and issue a shipping order and loading documents to the carrier when requested to load them from the port of origin or its depots;

4/ keep data and submit reports to the Authority regarding the type, quantity and purchase price of petroleum products daily loaded from the port of origin or its depots;

5/sell price regulated petroleum products at the rate set by the appropriate government body;

6/ keep data regarding his activities and submit reports to the Authority in writing or through other established

CamScanner

Made with Xodo PDF Reader and Editor

ስርዓት መሠረት ለባለሥልጣኑ ሪፖርት የማቅረብ፣

ፃ/ በባለሥልጣኑ የሚጠየቁ መስፈርቶችን አሟልቶ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የመያዝ፣

፰/በዚህ አዋጅ መሠረት በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ እና ደንቡን ለማስፈፀም በሚወጣ መመሪያ የሚወሰኑ ሌሎች ተዛማጅ ግዴታዎችን የማክበር፡፡

7/comply with the requirements of the Authority and hold a certificate of qualification;

8/ observe such other related obligations determined by a Regulation issued by the Council of Ministers and by a Directive.

፭.የኢትዮጵያ ነዳጅ አቅራቢ ድርጅት ግዴታዎች

የኢትዮጵያ ነዳጅ አቅራቢ ድርጅት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬ ከተመለከቱት በተጨማሪ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

፩/ ባለሥልጣኑ በሚወስነው መሠረት ሀገሪቱ በመጠባበቂያነት ልትይዘው የሚገባውን የነዳጅ መጠን የማከማቸትና የማስተዳደር፣

፪/በመርከብ መዘግየትም ሆነ በሌሎች የተለያዩ ምክንያቶች የነዳጅ አቅርቦቱ ሲቀንስ ወይም ሲስተጓጎል ከመጠባበቂያ ክምችት እንዲወጣ የሚያስፈልገውን ነዳጅ መጠን ለባለስልጣኑ የማሳወቅ እና ሲፈቀድም የማሰራጨትና የወጣውንም ነዳጅ እንዲተካ የማድረግ፣

5. **Obligations of Ethiopian Petroleum Supply Enterprise**

Ethiopian Petroleum Supply Enterprise shall, in addition to the obligations specified under Article 4 of this Proclamation, have obligations to:

1/ store and administer national reserve of petroleum products based on the direction of the Authority;

2/ notify to the Authority the amount of petroleum products necessary for distribution when the supply is reduced or disrupted due to the delay of ships or other reasons and distribute same upon approval and cause the reinstatement of such reserve;

CamScanner

Made with Xodo PDF Reader and Editor

፫/ በየአመቱ እያደገ የሚሄደውን የሃገሪቱን የነዳጅ ውጤቶች ፍላጎት መሠረት በማድረግ የማከማቸትና የመጫን አቅሙን የማሳደግ።

፮.የአከፋፋይ ግዴታዎች

ማንኛውም አከፋፋይ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

፩/ ጀማሪ ከሆነ በሥሩ ቢያንስ አምስት መቶ ሺ ሊትር የነዳጅ ውጤቶች በክምችት መያዝ የሚችል ዴፖ እና ፬ ማደያዎችን ይዞ ሥራ የመጀመር እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከተሰጠው ቀን ጀምሮ በሦስት ዓመታት ውሥጥ ተጨማሪ ፮ ማደያዎች የመገንባት፤

፪/ነባር ከሆነ ይህ አዋጅ ከጸናበት ቀን ጀምሮ በሁለት ዓመታት ውስጥ ቢያንስ አምስት መቶ ሺ ሊትር የነዳጅ ውጤቶች በክምችት መያዝ የሚችል ዴፖ እና ፬ ማደያዎች እንዲሁም በተከታዮቹ ሦስት ዓመታት ውሥጥ ተጨማሪ ፮ ማደያዎች የመገንባት፤

፫/የነዳጅ ውጤቶችን ከባዕድ ነገሮች ጋር ያለመቀላቀል እና ጥራቱን ሊያጓድል ከሚችል ማናቸውም ድርጊት የመቆጠብ፤

3/ upgrade its storage and loading capacity based on annual demand growth of petroleum products of the country.

6. Obligations of a Distributer

Any distributer shall have the following obligations to:

1/ commence operation with a depot that can store at least five hundred thousand liters of petroleum products and four fuel stations, and construct additional six fuel stations within three years from the date of the issuance of Certificate of Competence if he is a beginner;

2/ construct a depot that can store at least five hundred thousand liters of petroleum products and four fuel stations within two years from the effective date of this Proclamation and to have additional six fuel stations within the following three years if it is an existing distributer;

3/ refrain from committing adulteration and any other activities that degrade the quality of petroleum products;

CamScanner

Made with Xodo PDF Reader and Editor

፬/ ለነዳጅ ማደያዎች እና ለተጣራ ተጠቃሚዎች የነዳጅ ውጤቶችን በጅምላ የማከፋፈል፣

፭/የዋጋ ቁጥጥር የሚደረግባቸውን የነዳጅ ውጤቶች አግባብነት ያለው የመንግሥት አካል በሚወስነው ዋጋ የመሸጥ፣

፮/አጓጓዡ የተረከባቸውን የነዳጅ ውጤቶች በተፈለገው መዳረሻ ማራገፉን የማረጋገጥ፣

፯/ በሥሩ የሚሠራ ማንኛውም የነዳጅ ማደያ የተረከባቸውን የነዳጅ ውጤቶች ለመጨረሻ ተጠቃሚዎች በአግባቡ ማሠራጨቱን የመከታተል፣

፰/ በማከማቻ ዴፖው የተራገፈውን፣ ያሠራጨውን እና በቀሪነት የሚገኘውን የነዳጅ ውጤቶች መጠን መረጃ በመያዝ በጽሑፍ ወይም በሚዘረጋ የቴክኖሎጂ የአሰራር ስርዓት መሠረት ለባለሥልጣኑ በየወሩ መጨረሻ ሪፖርት የማቅረብ፣ እና

፱/ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ እና በመመሪያ የሚወሰኑ ሌሎች ተዛማጅ ግዴታዎችን የማክበር።

4/ distribute petroleum products in wholesale to fuel stations and direct users;

5/ sell price regulated petroleum products at the rate set by the appropriate government body;

6/ ensure that the carrier has unloaded petroleum products at the premises of the desired destination;

7/ follow up that any fuel station working under it has properly delivered petroleum products to end users;

8/ keep data regarding petroleum products loaded, distributed and remaining at petroleum depots and submit report at the end of every month to the Authority in writing or through other established electronic communication systems; and

9/ observe such other related obligations determined by a Regulation to be issued by the Council of Ministers and by a Directive issued hereunder.

፯. <u>የነዳጅ ማደያ ግዴታዎች</u>

ማንኛውም የነዳጅ ማደያ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

7. <u>Obligations of Fuel Stations</u>

Any fuel station shall have the obligations to:

CamScanner

Made with Xodo PDF Reader and Editor

ፈ) ለሚያቋቁመው ለእያንዳንዱ የነዳጅ ማደያ በባለሥልጣኑ የሚጠየቁ መሥፈርቶችን አሟልቶ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የማግኘት፣

ፉ) የነዳጅ ውጤቶችን በችርቻሮ ለመሸጥ የሚጠቀምባቸውን መሳሪያዎች የማስመርመር እና ሌሎች በዚህ አዋጅ መሠረት በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ እና በመመሪያ የሚወሰኑ ቁሳቁሶችን አሟልቶ የመሥራት፤

ፊ) የሚመለከተው የመንግስት አካል በአግባቡ የሚሠሩ ስለመሆናቸው ማረጋገጫ የሰጠባቸውን የነዳጅ ውጤቶች መቅጃ መሳሪያዎች ልኬት ሊያዛባ ከሚችል ማናቸውም ድርጊት የመቆጠብ፤

ፋ) የነዳጅ ውጤቶችን ውል ከገባው አከፋፋይ ብቻ በመግዛትና በመረከብ ነዳጅ ማደያው ውስጥ እንዲራገፍ የማድረግ እና ስለተራገፈው ነዳጅ በጽሑፍ ወይም በሚዘረጋው የቴክኖሎጂ የአሠራር ሥርዓት መሠረት ለአጓጓዡ፣ ለአከፋፋዩ እና ለባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ላለው አካል ተገቢውን መረጃ የመስጠት፤

ፌ) የነዳጅ ውጤቶችን ከባዕድ ነገሮች ጋር ያለመቀላቀል፣ ጥራቱን ሊያጓድል ከሚችል ማናቸውም ድርጊት የመቆጠብ እና ለመጨረሻ ተጠቃሚዎች በችርቻሮ የመሸጥ፤

1/ obtain a certificate of competence for each fuel station upon the fulfillment of the Authority;

2/ cause the regular inspection of the equipment used to retail petroleum products and operate by fulfilling other materials determined by a Regulation to be issued by the Councile of Ministers and Directive issued here under;'

3/ refrain from any act that may distort the measurement of recording devices of petroleum products verified by the relevant government body;

4/ buy and receive petroleum products only from the contracting distributor, unload them at the fuel station and provide appropriate information to the carrier, the distributor and the Authority or the Relevant Body in writing or through the established electronic communication system;

5/ refrain from committing adulteration and any other acts that degrade the quality of petroleum products and sell them to the end users in a retail trade;

CamScanner

Made with Xodo PDF Reader and Editor

፮/ የሞጋ ቁጥጥር የሚደረግባቸውን የነዳጅ ውጤቶች አግባብነት ያለው የመንግሥት አካል በሚወስነው ሞጋ የመሸጥ፣

፯/ ለመጨረሻ ተጠቃሚዎች ያለተቆራረጠ የሃያ አራት ሰዓት የሽያጭ አገልግሎት የመስጠት፣

፰/ነዳጅ በማደያ ውስጥ እያለ የሽያጭ አገልግሎት ያለማቋረጥ፣

፱/ ከነዳጅ ውጤቶች ግብይት ጋር የተያያዙ መረጃዎችን በአግባቡ አደራጅቶ የመያዝና ሲጠየቅም ለባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ላለው አካል የማቅረብ፣

፲/ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብና በመመሪያ የሚወሰኑ ሌሎች ተዛማጅ ግዴታዎችን የማክበር።

፰.የአንቺዎር ግዴታዎች

ማንኛውም የነዳጅ ውጤቶች አንቺዎር የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

፩/ ማንቀሳቀሻውን በሚመለከተው የመንግሥት አካል በየአመቱ የሚስመረመርና የጸና የካሊብሬሽን የምስክር ወረቀት የመያዝ፣

፪/ ከነዳጅ ውጤቶች በስተቀር በማንቀሳቀሻው ሌሎች ማናቸውንም ሞኖዎች አለማንቀሳቀስ፣

6/ sell price regulated petroleum products at the rate set by the Relevant Government Body;

7/ provide uninterrupted twenty-four hours service to the end users;

8/ uninterrupted sales service while fuel is in the Fuel Station;

9/ keep data related to the marketing of petroleum products and provide to the Authority or the Relevant Body upon request;

10/observe such other related obligations determined by directives issued hereunder.

8. Obligations of the Carrier

Any carrier of petroleum products shall have the obligations to:

1/ cause the inspection of the means of transportation every year by an appropriate government body and hold a valid calibration certificate;

2/ refrain from carrying any other cargo except petroleum products;

CamScanner

Made with Xodo PDF Reader and Editor

ሸ/ አስመጪው የሚሰጠውን የማጓጓዣና የጭነት ሰነዶች በመያዝ እንዲያጓጉዝ በተፈቀደለት መስመር ብቻ የማጓጓዝ፤ በተቆጣጣሪ አካላት ሲጠየቅም ሰነዶቹን የማሳየት፤

ቀ/ የጫነውን የነዳጅ ውጤት ከአከፋፋይ ጋር በገባው ውል መሠረት በተመደበለት መዳረሻ የማራገፍ እና የማስረከብ፤

በ/ በማጓጓዝ ሂደት እንደውሉ ለመፈጸም የሚያስችሉ ወይም ሌላ ማንኛውም አይነት ሂደቱን የሚያስተጓጉሉ ሁኔታዎች ካጋጠመው ለባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ላለው አካል የማሳወቅ እና በሚሰጠው ትእዛዝ መሠረት የመፈጸም፤

ተ/ ከነዳጅ ማጓጓዝ ጋር የተያያዙ መረጃዎችን የመያዝና በጽሑፍ ወይም በሚዘረጋ የቴክኖሎጂ የአሰራር ስርዓት መሠረት ለባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ላለው አካል ሪፖርት የማቅረብ፤

ቸ/ማንኛውም የነዳጅ ውጤቶች አጓጓዥ ተሽከርካሪ ጂፒኤስ የመግጠም ግዴታ አለበት፤

ኀ/ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብና በመመሪያ የሚወሰኑ ሌሎች ተዛማጅ ግዴታዎችን የማክበር።

3/ carry the shipping and cargo documents provided by the importer, transport only at the permitted route and show the documents when requested by regulatory bodies;

4/ transport and deliver petroleum products at the premises of the desired destination according to the contract made with the distributer;

5/ notify to the Authority or the Relevant Body and perform according to the direction given to him where he faces any conditions that prevent him to perform in accordance with the contract or any other problem during the transportation process;

6/ keep data related to the transportation of petroleum products and submit reports to the Authority or to the Relevant Body in writing or through other established electronic communication systems;

7/ To enforce GPS in petroleum transportation,;

8/ respect such other related obligations determined by a Regulation to be issued by the Councile of Ministers and by a Directive issued hereunder.

CamScanner

Made with Xodo PDF Reader and Editor

፱. የቀጥታ ተጠቃሚ ግዴታዎች

ማንኛውም የቀጥታ ተጠቃሚ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

፩/ በመመሪያ በሚወሰነው መሠረት የቀጥታ ተጠቃሚ ለመሆን የሚያበቁ መስፈርቶችን በማሟላት ለባለሥልጣኑ ማመልከቻ አቅርቦ ፈቃድ የማግኘት፤

፪/ የተፈቀደለትን የነዳጅ ውጤቶች አይነት እና መጠን ከአከፋፋይ በመግዛት ለተፈቀደለት ፕሮጀክት ወይም የመንግሥት የልማት ድርጅት ዓላማ ብቻ የመጠቀም፤

፫/ የተረከባቸውን የነዳጅ ውጤቶች አጠቃቀም በተመለከተ መረጃ በመያዝ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ መመሪያ በሚወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ በጽሑፍ ወይም በሚዘረጋ የቴክኖሎጂ የአሠራር ሥርዓት መሠረት ለባለሥልጣኑ ሪፖርት የማቅረብ፤

፬/በማንኛውም ምክንያት የቀጥታ ተጠቃሚ መሆኑን ሲያቋርጥ ይህንኑ በጽሑፍ ወይም በሚዘረጋ የቴክኖሎጂ የአሠራር ሥርዓት መሠረት በ፲፭ ቀናት ለባለሥልጣኑ እና የነዳጅ ውጤቶችን ሲያስረክበው ለነበረው አከፋፋይ የማሳወቅ እና የተሰጠውን ፈቃድ ለባለሥልጣኑ የመመለስ፤

9. Obligations of Direct Users

Any direct user shall have the obligations to:

1/ submit an application to the Authority and obtain permission of direct user upon the fulfillment of the requirements specified by Directives issued in accordance with this Proclamation;

2/ buy the permitted type and amount of petroleum products from a distributer and use them only for the purpose of the permitted project or government enterprise;

3/ keep data regarding the utilization of petroleum products and submit a report to the Authority in writing or through other established electronic communication system within a period specified by Directives issued hereunder;

4/notify to the Authority and its distributor in writing or through other established electronic communication systems and return the permit to the Authority with in 15 days when he ceases to be a direct user due to any reason;

CamScanner

Made with Xodo PDF Reader and Editor

፰/ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ መመሪያ የሚወሰኑ ሌሎች ዝርዝር የአጠቃቀም ሁኔታዎችን የማክበር፣፣

ክፍል ሦስት
ስለ ተቆጣጣሪ አካላት፣ ስለብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እና ስለግንባታ ፈቃድ

፲.የሚኒስቴሩ ሥልጣንና ተግባር

ሚኒስቴሩ በሌሎች ሕጎች የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ የታችኛውን የነዳጅ ንዑስ ኢንዱስትሪ ልማት የሚያሳልጡ ጥናትና ምርምሮችን ያካሂዳል፣ፖሊሲዎችና ሕጎችን ያዘጋጃል፣ ሲጸድቁም አፈጻጸማቸው ይከታተላል፣ በዘርፉ መንግስትን ያማክራል፣

፪/ የነዳጅ ግብይት ቁጥጥር እና አጠቃቀም ሥርዓትን በበላይነት ይመራል፣

፫/ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚረዱ ረቂቅ መመሪያዎችን ያዘጋጃል፡፡

፲፩.የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር

ባለሥልጣኑ በሌሎች ሕጎች የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት

5/comply with other terms and conditions of use specified by Directives issued in accordance with this Proclamation.

PART THREE
REGULATORY BODIES, CERTIFICATES OF COMPETENCE AND CONSTRUCTION PERMITS

10. Powers and Duties of the Ministry

Without prejudice to the powers and duties given by other laws, the Ministry shall have the powers and duties to:

1/ conduct policies and laws that promote the lower fuel submitory of the fuel, follows the implementation of their performance and advises the government in the field;

2/ leads petroleum marketing and use operation;

3/ approves draft Directives that help to enforce this Proclamation.

11. Powers and Duties of the Authority

Without prejudice to the powers and duties given by other laws, the Authority shall have the powers and duties to:

CamScanner

Made with Xodo PDF Reader and Editor

ይኖሩታል፡-

፩/ተጠቃሚዎችን እና አካባቢውን ማዕከል በማድረግ የብቃት ማረጋገጫ መስፈርት አዘጋጅቶ የነዳጅ ማደያዎችን ከፍተኛ፣ መካከለኛና አነስተኛ ደረጃ በማለት ይመድባል፣ የተሰጣቸውን ደረጃ መሠረት በማድረግ የሚቋቋሙበትንና የሚሠሩበትን አካባቢ ከክልሎች እና ከሁለቱም ከተማ አስተዳደሮች ጋር በመሆን ይወስናል፣

1/ Classify Fuel stations as large, medium and small level by setting the criteria of competence taking users and the environment in to account and determine their establishment and working area in collaboration with the Regions and the two City Administrations based on such level;

፪/ ለግብይት ተዋናዮች የብቃት ማረጋገጫ መስፈርት ማዘጋጀትና መስፈርቱን ማሟላታቸውን በማረጋገጥ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትና የግንባታ ፍቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፣

2/ issue a certificate of competence and a construction permit to market actors ensuring the fulfillment of the requirements specified; monitor their implementaion;

፫/ ማንኛውም አከፋፋይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) መሠረት ለሚገነባው ዴፖ እና የነዳጅ ማደያ ሀጋዊ ፈቃድ ባለው አማካሪ የፕሮጀክት ጥናትና የድርጊት መርሐ-ግብር አዘጋጅቶ እንዲያቀርብ በማድረግና ገምግሞ በማጽደቅ የግንባታ ፈቃድ ይሰጣል፣ በመርሐ-ግብሩ መሠረት መከናወኑን ይከታተላል፣

3/ issue a construction permit to a distributer for the construction of depots and Fuel Stations to be constructed pursuant to sub article (1) and (2) of Article 6 of this Proclamation upon the review and approval of a project study and action plan prepared by a legally licensed consultant and follow-up its implementation;

፬/የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ወይም የግንባታ ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርቡ ማመልከቻዎችን ሲመረምር ከሚመለከታቸው አስፈጻሚ አካላት ጋር በመመካከር በግብይት ሰንሰለት ውስጥ የህብረተሰቡን ጤንነትና

4/ ensure that safety precautions necessary to protect the health and safety of the community and the environment are met in the marketing chain by consulting with the relevant executive bodies when examining applications for certificate of

CamScanner

Made with Xodo PDF Reader and Editor

ደህንነት ለመጠበቅና የአካባቢ ጥበቃን ለማረጋገጥ የሚረዱ የደህንነት ጥንቃቄ መስፈርቶች መሟላታቸውን ያረጋግጣል፤

ሯ/ የሀገሪቱን የነዳጅ ውጤቶች ፍላጎት መጠን በማጥናት አመታዊ የነዳጅ አቅርቦት ጣሪያን ለነዳጅ አስመጪ ያሳውቃል፤ በወደቀው ዕቅድ መሠረት የግዥ ሂደቱን ተከትሎ መገዛቱንና በመርሐ-ግብሩ መሠረት ወደ ወደብ ተርሚናል መግባቱን ይከታተላል፤

ሱ/ አማራጭ የግብይት አሠራሮችን ይዘረጋል፤

ሷ/ የነዳጅ ውጤቶች ግብይት የቁጥጥር ስርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊነቱን ያረጋግጣል፡፡

ቷ/የግብይት ተዋናዮችን የውል ስምምነት ሰነድ እና የሪፖርት አቀራረብ ፎርማቶች ይመለከታል፤አፈጻጸማቸውንም ይቆጣጠራል፡፡

ቧ/ ከነዳጅ ውጤቶች ግብይት ጋር በተያያዘ ሕገ ወጥ ድርጊት በፈፀመ የግብይት ተዋናይ ላይ በዚህ አዋጅ፣ በአዋጁ መሰረት በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብና በመመሪያዎች መሠረት አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፤

ቨ/ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ በሚወሰን ተመን መሠረት የአገልግሎት ክፍያ ያስከፍላል፤

competence or construction permit;

5/ notify to the importer the annual supply ceiling of petroleum products based on the study of the country's demand, follow-up the procurement process and its delivery into the port terminal according to the schedule;

6/ put in place alternative marketing frameworks;

7/establish a controlling system for the marketing of petroleum products,

8/consider the contract documents and reporting formats of marketing actors, and oversee their implementation.

9/take administrative measures against any market actor who has committed an illegal act in accordance with this Proclamation, a Regulation to be issued by the Councle of Ministers and a Directive issued in accordance with this Proclamation hereunder;

10/charge fees for the services it renders in accordance with the rate determined by a Regulation to be issued by the Council of Ministers;

CamScanner

Made with Xodo PDF Reader and Editor

፲፩/ ለነዳጅ ውጤቶች ግብይት አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተባማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

11/perform other related activities necessary for the marketing of petroleum products.

፲፪.አግባብ ያለው አካል ሥልጣንና ተግባር

12. Powers and Duties of the Relevant Body

አግባብ ያለው አካል የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

The Relevant Body shall have the powers and duties to:

፩/አንገቡ ከአከፋፋይ ስለተረከበው የነዳጅ ውጤቶች መጠን እና በማደያዎች በአግባቡ ስለማራገፉ እንዲሁም ሌሎች ለመስኩ ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያደራጃል፣ ለሚመለከታቸው አካላት ያሰራጫል፣

1/ collect organize and disseminate to the concerned bodies the amount of petroleum products that the carrier received from the distributor and unloaded to the Fuel Stations as well as other relevant information of the sector;

፪/ የነዳጅ ውጤቶች በክልሉ ውስጥ በሀጋዊ መንገድ ስለመጓጓዛቸው፣ስለመሰራጨታቸው እና መንግሥት በሚወስነው የችርቻሮ መሸጫ ዋጋ መሠረት ስለመሸጣቸው ቁጥጥር ያደርጋል፣

2/control whether petroleum products in Regions are transported, distributed and sold in accordance with the retail price set by the relevant government body;

፫/ የነዳጅ ማደያዎች ለመጨረሻ ተጠቃሚዎች በፍላጎታቸው እና በከፈሉት ዋጋ ልክ አገልግሎት መስጠታቸውን ያረጋግጣል፣

3/ensure that fuel stations provide service to the end users in accordance with their demand and the price they pay;

፬/ ነዳጅ ማደያዎች በሌሉባቸው አካባቢዎች የነዳጅ ግብይት ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ እና መመሪያ መሰረት መከናወኑን ይቆጣጠራል፣

4/give a written permission when it is deemed necessary to sell petroleum products in a barrel or similar containers at a place where there is no accessible Fuel Stations, and control that its implementations carried out in accordance with Directives issued in accordance with this Proclamation;

CamScanner

Made with Xodo PDF Reader and Editor

ሸ/ የነዳጅ ውጤቶች ከባዕድ ነገሮች ጋር ሳይቀላቀሉ ጥራታቸውን ጠብቀው ለመጨረሻ ተጠቃሚዎች መቅረባቸውን ይቆጣጠራል፣ ጥራታቸው ተጓድሎ ሲገኝም በህግ አግባብ እርምጃ ይወስዳል፣

ሽ/ተቆጣጣሪዎችን በመመደብ በክልሉ የሚካሄደውን የነዳጅ ውጤቶች ግብይት ይቆጣጠራል፣

ቀ/ በክልሉ የሚካሄደውን የነዳጅ ውጤቶች ግብይት መረጃ በማሰባሰብ፣ በመተንተን እና በማጠናቀር ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፣ሲወሰንም አፈጻጸሙን ይከታተላል፣

ቐ/ የነዳጅ ውጤቶች ግብይትን በተመለከተ ከባለሥልጣኑ ጋር የመረጃ ልውውጥ ያደርጋል፣

ቒ/ በክልሉ ለሚካሄድ የነዳጅ ውጤቶች ግብይት አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል።

፲፫. ስለብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ

፩/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠ የጸና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይኖረው በነዳጅ ውጤቶች ግብይት ሥራ ላይ መሠማራት አይችልም።

፪/ በነዳጅ ውጤቶች ግብይት መሠማራት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው አስፈላጊውን ቅድመ ሁኔታ በማሟላት የብቃት

5/control that petroleum products delivered to end users are not adulterated and take measures in accordance with the law where substandard products are delivered;

6/assign competent inspectors and control the marketing of petroleum products in the Region;

7/collect, analyze and organize data relating to the marketing of petroleum products in the Region, submit same to the appropriate body and follow-up its implementation upon approval;

8/exchange information with the Authority regarding the marketing of petroleum products;

9/ perform such other activities related to the marketing of petroleum products in the Region.

13. Issuance of Certificate of Competence

1/ No person can engage in the marketing of petroleum products without having a valid certificate of competence issued in accordance with this Proclamation.

2/ Any person who desires to engage in the marketing of petroleum products may file a written application to the

CamScanner

Made with Xodo PDF Reader and Editor

ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ለባለሥልጣኑ በጽሁፍ ማመልከቻ ማቅረብ አለበት።

ፐ/ማመልከቻ የሚቀርብበት፣ የሚገመገምበት፣ ተቀባይነት የሚያገኝበት እና የሚከለከልበት ሥርዓት እንዲሁም መሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች፣ መቅረብ የሚገባቸው መረጃዎችና ማስረጃዎች በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ መመሪያ የሚወሰኑ ይሆናል።

ፒ/ ባለሥልጣኑ የቀረበው ማመልከቻ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) መሠረት የተሟላ ሆኖ ሲያገኘው ማመልከቻው በደረሰው በ፴ (ሰላሳ) የሥራ ቀናት ውስጥ የተጠየቀውን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ የተጠየቀውን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የከለከለ ከሆነ ምክንያቱን ለአመልካቹ በጽሑፍ መግለጽ አለበት።

Authority requesting a certificate of competence upon thefulfillment of the necessary requirements.

3/The procedure for the submission, evaluation, acceptance and rejection of an application, as well as the conditions to be met, the information and evidence required shall be determined by Directives issued in accordance with this Proclamation.

4/ The Authority shall issue the requested certificate of competence within 30 (thirty) working days from the receipt of the application when it is satisfied that the application is complete in accordance with sub-article (2) and (3) of this Article, If it rejects the application for the request of the certificate of competence the Authority shall explain the reason in writing to the applicant.

፲፬.የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ፀንቶ የሚቆይበት እና የሚታደሥበት ሁኔታ

14.Validity and Renewal of Certificate of Competence

፩/ ለማንኛውም የግብይት ተዋናይ የተሰጠው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለሶስት ዓመት ፀንቶ የሚቆይ ይሆናል። የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ በየሶስት ዓመቱ ማብቂያ ሁለት ወር ሲቀረው ጀምሮ መታደስ አለበት።

1/ The certificate of competency issued to any marketing actor will be valid for 3 years.The certificate of competency must be renewed 2 months before the end of every 3 years.

CamScanner

Made with Xodo PDF Reader and Editor

፪/ ለእድሳት የሚያስፈልጉ መስፈርቶችና ተያያዥ ጉዳዮችን በተመለከተ ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብና በመመሪያ ይወሰናል።

፲፭. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትን ስለማስተላለፍ

የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትን ለሌላ ሰው ማስተላለፍ አይቻልም።

፲፮.የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትን ስለማገድ ወይም ስለመሠረዝ

፩/ ማንኛውም የግብይት ተዋናይ የአካባቢ ጥበቃን፣ የማህበረሰብ ደህንነትን፣ የአከፋፋይ አነስተኛ የነዳጅ ውጤቶች የማከማቸት አቅምንና በሥሩ የሚተዳደሩ የነዳጅ ማደያዎች ቁጥርን፣ የነዳጅ ውጤቶች ጥራት ደረጃን፣ የተዘረጋ የግብይት ሥርዓትን፣ ታክስ ማጭበርበርን ወይም ሌሎች ግዴታዎችን አስመልክቶ በዚህ አዋጅም ሆነ በሌላ ሕግ የወጡ ድንጋጌዎችን ተላልፎ ከተገኘ ጉድለቶቹን እስኪያስተካክል ድረስ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ ይታገዳል።

፪/ ባለሥልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር

2/ The standard as well as the conditions for the renewal of the certificate of competence shall be determined by Regulation to be issued by the Councile of Ministers and by a Directive issued hereunder.

15. Transfer of Certificate of Competence

Certificate of competence may not be transferred to another person .

16. Suspension or Cancellation of Certificate of Competence

1/ A certificate of competence shall be suspended until the market actor corrects the deficiencies if he has violated the provisions of this Proclamation or any other law relating environmental protection, community safety, the minimum storage capacity and the number of Fuel Stations required under the distributer, the quality standard of petroleum products, established marketing system, tax evasion or any other obligations.

2/ The Authority shall notify the market actor in writing the reason for the

CamScanner

Made with Xodo PDF Reader and Editor

ወረቀቱ የታገደበትን ምክንያት በሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ ጉድለቶቹን ለማስተካከል ሊወሰድ ስለሚገባው እርምጃ ለግብይት ተዋናዩ በጽሁፍ ያሳውቀዋል።

፫/ የግብይት ተዋናዩ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጉድለቶቹን አስተካክሎ እገዳው እንዲነሳለት ማመልከቻ ካቀረበ ባለሥልጣኑ እገዳውን ያነሳል።

፬/ የግብይት ተዋናዩ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጉድለቶቹን ካላስተካከለ ባለሥልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን ይሰርዘዋል።

3/The Authority shall withdraw the suspension if the market actor submits an application for the lifting of the suspension by correcting the deficiencies within the prescribed period of time.

suspension of the certificate of competence and the corrective measures to be taken within three months time.

4/The Authority shall cancel the certificate of competence if the market actor failed to correct the deficiencies within the prescribed period of time.

፲፯.ስለግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ

፩/ ማንኛውም የግብይት ተዋናይ በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠ የጸና የግንባታ ፈቃድ ሳይኖረው የነዳጅ መሠረተ ልማት ግንባታ ማካሄድ አይችልም፣ ሆኖም በአንድ ነባር የነዳጅ ተቋም ውስጥ ለሚካሄድ መደበኛ የጥገና ሥራዎች የግንባታ ፈቃድ ማውጣት አያስፈልግም።

፪/ የግንባታ ፈቃድ ለማግኘት የሚፈልግ የግብይት ተዋናይ ባለሥልጣኑ የሚያዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት የሚከተሉትን ሰነዶች አያይዞ ማቅረብ አለበት፡-

17. Issuance of Construction Permit

1/ No market actor can undertake construction work of petroleum infrastructure without having a valid construction permit issued in accordance with this Proclamation; however a construction permit is not required for regular maintenance works in an existing petroleum facility.

2/ A market actor who desires to have a construction permit may file the application form prepared by the Authority with the following annexes:

CamScanner

Made with Xodo PDF Reader and Editor

ሀ) የነዳጅ መሠረተ ልማት የፕሮጀክት ጥናትና የድርጊት መርሀ ግብር፣

ለ) አግባብ ባለው የአካባቢ ጥበቃ መሥሪያ ቤት ይሁንታ የተሰጠው የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት፣

ሐ) የነዳጅ መሠረተ ልማቱ ማህበራዊ ፋይዳና ኢኮኖሚያዊ አዋጭነት ጥናት፣

መ) የግንባታ ፕላንና ዝርዝር መሥፈርት፣

ሠ) የሚገነባው የነዳጅ ቧንቧ መሥመር ዝርጋታ ከሆነ መነሻውን እና መድረሻውን የሚያሳይ ፕላን እና አግባብ ባለው የመንግሥት አካል የተሰጠ የቧንቧ መሥመሩ የሚያልፍበትን መሬት የመጠቀም ፈቃድ፣

ረ) በዚህ አዋጅ መሠረት በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የተገለፁ ሌሎች ዝርዝር መረጃዎች።

a) Petroleum Infrastructure Project Study and its Action Plan;

b) an environmental impact assessment study approved by the appropriate environmental protection Authority;

c) The study of social benefits and economic viability of the petroleum infrastructure;

d) construction plans and specifications;

e) where it is a pipeline construction, the Plan indicating the departure and destination as well as the land use permit issued by the appropriate government body;

f) other particulars specified in the Regulations and Directives issued in accordance with this Proclamation.

፫/ ባለሥልጣኑ የቀረበውን ማመልከቻ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የተሟላ ሆኖ ሲያገኘው ማመልከቻው በደረሰው በ፴ (ሰላሳ) የሥራ ቀናት ውስጥ የተጠየቀውን የግንባታ ፈቃድ ይሰጣል፣ የከለከለ ከሆነ ምክንያቱን በዚሁ ቀን ለአመልካቹ በጽሑፍ

3/ the Authority shall issue the requested construction permit within 30 (thirty) working days from the receipt of the application when it is satisfied that the application is complete pursuant to sub-article (2) of this Article, the Authority

CamScanner

Made with Xodo PDF Reader and Editor

መግለጽ አለበት፡፡

፲፰.የግንባታ ፈቃድ የሚያበቃበት ጊዜ

፩/ የነዳጅ ተቋም ግንባታ ፈቃድ በተሰጠ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ የተፈቀደው የግንባታ ሥራ ካልተጀመረ ፈቃዱ ይሰረዛል፡፡

፪/ የነዳጅ ተቋም ግንባታ ፈቃድ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ በአንድ ዓመት ከስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ግንባታው ተጠናቆ ሥራ መጀመር አለበት፡፡

፲፱.የግንባታ ፈቃድን ስለማገድ ወይም ስለመሠረዝ

፩/ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ፣ በአዋጁ መሠረት በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች ወይም በሰጠው የግንባታ ፈቃድ የተመለከቱት ግዴታዎች ወይም ገደቦች ያልተከበሩ መሆኑን ሲያረጋግጥ ፈቃዱን ማገድ ይችላል፡፡

፪/ባለሥልጣኑ ፈቃዱ የታገደበትን ምክንያት እና ተገቢ በሆነ የጊዜ ገደብ ውስጥ ጉድለቶቹን ለማስተካከል ሊወሰድ ስለሚገባው እርምጃ ለግብይት ተዋናዩ በጽሁፍ ያሳውቀዋል፡፡

፫/ የግብይት ተዋናዩ በተሰጠው የጊዜ ገደብ

shall explain the reason in writing to the applicant if it denies the requested construction permit.

18. Construction permit expiration Date

1/ If the approved construction work is not started within six months after the petroleum facility construction permit is issued, the permit will be revoked.

2/ The construction of the petroleum facility must be completed and work started within one year and six months from the date of approval.

19. Suspension or Cancellation of Construction Permit

1/ The Authority may suspend the construction permit when it is satisfied that the obligations specified in this Proclamation, Regulations and Directives issued in accordance with this Proclamation or the conditions in the construction permit are not complied with.

2/ The Authority shall notify the market actor in writing the reason for the suspension of the permit and the corrective measures to be taken within a reasonable period of time.

3/ The Authority shall withdraw the suspension if the market actor

CamScanner

Made with Xodo PDF Reader and Editor

ውስጥ ጉድለቶቹን አስተካክሎ እገዳው እንዲነሳለት ማመልከቻ ካቀረበ ባለሥልጣኑ እገዳውን ያነሳል።

፬/ የግብይት ተዋናዩ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጉድለቶቹን ካላስተካከለ ወይም ፈቃዱ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በ፲፪(አስራሁለት) ወራት ውስጥ የግንባታ ሥራውን ካልጀመረ ባለሥልጣኑ የሰጠውን የግንባታ ፈቃድ ይሰርዛል።

ክፍል አራት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፳. ስለዲጂታል የግብይት ሥርዓት

፩/ማንኛውም የግብይት ተዋናይ የነዳጅ ውጤቶች ግብይት ክፍያውን በባለሥልጣኑ ዕውቅና በተሰጠው በዲጂታል የክፍያ ሥርዓት መፈፀም አለበት።

፪/ ማንኛውም የግብይት ተዋናይ ባለሥልጣኑ በየጊዜው የሚዘረጋውን እና በህዝብ ማስታወቂያ የሚያሳውቀውን ዲጂታል የግብይት ሥርዓት ተግባራዊ የማድረግ ግዴታ አለበት።

፳፩. ማደያ በሌለባቸው አካባቢዎች ስለሚፈጸም የነዳጅ ግብይት

ማደያ በሌለባቸው አካባቢዎች የሚፈጸም

submits an application for the lifting of the suspension by correcting the deficiencies within the prescribed period of time.

4/ The Authority shall cancel the construction permit if the market actor failed to make the required corrective measures within the prescribed period of time or if the construction work is not started within 12 (twelve) months from the issuance of the permit.

PART FOUR
MISCELLANEOUS PROVISIONS

20. Digital Marketing System

1/ Any market actor shall make the transaction payment of petroleum products through the digital payment system recognized by the Authority.

2/ Any market actor shall implement the digital marketing system that the authority introduces and announces through public notice from time to time.

21. Retailing of Petroleum Products in Areas where Fuel Stations are not accessible

The retailing of petroleum products in

CamScanner

Made with Xodo PDF Reader and Editor

የነዳጅ ውጤቶች የችርቻሮ ግብይት ሥርዓት በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል።

areas where Fuel Stations are not accessible shall be determined by Directive issued in accordance with this Proclamation.

፳፪. ስለጠቋሚ

ሀገ-ወጥ የነዳጅ ውጤቶች ንግድ ወይም የኮንትሮባንድ ድርጊት የተፈጸመ መሆኑን ጠቁሞ ላስያዘ ሰው ጥቆማው ውጤታማ ሲሆን የጠቋሚ አበል በፐርሰንት ይከፈለዋል፣ ዝርዝሩ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።

22. **Informants**

Payment shall be made for informants who expose illegal trade or contraband offenses in percentage; particulars shall be determined accordance with the Regulation to be issued by the Council of Ministers.

፳፫. ስለአስተዳደራዊ እርምጃዎች

፩/ ባለሥልጣኑ ይህንን አዋጅ ወይም በአዋጁ መሠረት የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን ተላልፎ የተገኘ ማንኛውንም የግብይት ተዋናይ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ወይም የግንባታ ፈቃድ ሊያግድ ወይም ሊሰርዝ ይችላል።

23. **Administrative Measures**

1/ The Authority may suspend or cancel a Certificate of Competence or a construction of any market actor who violates the provisions of this Proclamation, Regulation to be issued by the Coincle of Ministers or Directives issued hereunder.

፪/ በዚህ አዋጅ፣ በአዋጁ መሠረት በሚኒስትሮች ምክር ቤት በወጡ ደንቦች ወይም በመመሪያዎች ስለ መረጃዎች አያያዝ ወይም ስለ ሪፖርት ማቅረብ የተደነገጉ ድንጋጌዎችን ተላልፎ የተገኘ የግብይት ተዋናይ በመጀመሪያ ጥፋት የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፣ በማስጠንቀቂያው መሠረት ተገቢውን ማስተካከያ ካላደረገ ወይም በድጋሚ

2/ The Authority shall issue a written warning to any market actor who violates the provisions of this Proclamation, Regulation to be issued by the Council of Ministers or Directives issued in accordance with this Proclamation relating record keeping or reporting requirements for the first time;

CamScanner

Made with Xodo PDF Reader and Editor

ተመሳሳይ ጥፋት ከፈጸመ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ ወይም የግንባታ ፈቃዱ ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ ይችላል።

failure to make the required corrections based on the written warning or committing a similar offense for the second time may cause the suspension or cancellation of a Certificate of Competence or a construction permit of the market actor.

፫/ ማንኛውም ነባር የግብይት ተዋናይ ይህ አዋጅ ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወራት ውስጥ መስፈርቶችን አሟልቶ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ካላገኘ የንግድ ፈቃዱ ይሰረዛል።

3/ The business license of any existing market actor shall be cancelled if he failed to obtain a certificate of competence within six months from the effective date of this Proclamation upon the fulfillment of the prescribed requirements.

፬/ ማንኛውም አከፋፋይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮ ንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) መሠረት የሚጠበቅበትን የነዳጅ ዴፖ እና ማደያዎች ካልገነባ የንግድ ፈቃዱ ይሠረዛል።

4/ The business license of any distributor shall be cancelled if he failed to construct a depot and Fuel Stations required under sub-article (1) and (2) of Article 6 of this Proclamation.

፭/ ከአከፋፋይ የተረከባቸውን የነዳጅ ውጤቶች ከተሰጠው ፈቃድ ዓላማ ውጪ ሲጠቀም የተገኘ የቀጥታ ተጠቃሚ ፈቃዱ ይሰረዛል፣ ከአምስት ዓመት በፊት ፈቃድ እንዲሰጠው ማመልከት አይችልም።

5/The permit of any direct user shall be cancelled if it is found using petroleum products out of the purpose of his permit and is not allowed to apply for such permit for the next five consecutive years.

፮/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትን ወይም የግንባታ ፈቃድን ለማገድ ወይም

6/Particulars for the suspension and cancellation of a Certificate of Competence or a construction permit under this Article shall be determined

CamScanner

Made with Xodo PDF Reader and Editor

ለመሰረዝ የሚያበቁ ዝርዝር መስፈርቶች በመመሪያ የሚወሰኑ ይሆናል።

by Regulations and Directives to be issued following this Proclamation.

፳፬. ስለቅሬታ አቀራረብ

፩/ በዚህ አዋጅና በአዋጁ መሠረት በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች በሚሸፈን ማናቸውም ጉዳይ ላይ ጉዳዩ በሚመለከተው የሥራ ኃላፊ በተሠጠ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው ውሳኔ በተሰጠ በ፲ (አስር) ተከታታይ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን እንደ ነገሩ አግባብነት ለባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ላለው አካል የበላይ ኃላፊ በጽሁፍ ማቅረብ ይችላል።

1/ Any person who is aggrieved with the decision of any concerned official regarding matters covered in this Proclamation, Regulations and Directives issued in accordance with this Proclamation may lodge his complaint in writing to the head of the Authority or the Relevant Body, as appropriate, within 10 (ten) consecutive days from the rendering of such decision.

፪/ የባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ያለው አካል የበላይ ኃላፊ ቅሬታው በደረሰው በ፲፭ (አስራ አምስት) የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ውሳኔ መስጠት አለበት።

2/The Head of the Authority or the Relevant Body shall notify his decision in writing to the aggrieved person within 15 (fifteen) working days from the receipt of the complaint.

፫/ ባለስልጣኑ ወይም አግባብ ያለው አካል የበላይ ኃላፊ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ለሚኒስቴሩ የቅሬታ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል።

3/ The complainant may lodge his complaint to the Ministry if he is aggrieved by the decision of the Head of the Authority or the Relevant Body.

፬/ ሚኒስቴሩ በሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ያለው ቅሬታ አቅራቢ ውሳኔው በተሰጠው በ፷ ተከታታይ ቀናት ውስጥ ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት አቤቱታ ማቅረብ ይችላል።

4/The complainant may lodge his complaint to the competent Court within 60 (sixty) consecutive days from the rendering of the decision if

CamScanner

Made with Xodo PDF Reader and Editor

፳፭ ስለ ወንጀል ቅጣት

፩/ የነዳጅ ውጤቶችን ከተፈቀደው ቦታ፡ ውጪ ያከማች፣ ሊሸጥ ከሚገባው ሰው፣ ቦታ፡ እና የግብይት ሥርአት ውጪ ሲሸጥ የተገኘ ወይም በመመሪያ በተወሰነው መሠረት አደጋ ያስከትላሉ በተባሉ መያዣዎች ሲሸጥ የተገኘ ማንኛውም ሰው የተያዘው የነዳጅ ውጤት ተወርሶ ከሶስት አመት እስከ አምስት አመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት እና ከብር ሦስት መቶ ሀምሳ ሺ. እስከ አምስት መቶ ሺ. በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል

፪/ የነዳጅ ውጤቶችን ሆን ብሎ ከባዕድ ነገሮች ጋር በመቀላቀል ለግብይት ያቀረበ ማንኛውም ሰው ነዳጁ እንዲወገድ ተደርጎ ከአምስት አመት እስከ ሰባት አመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት እና ከብር ሶስት መቶ ሀምሳ ሺ. እስከ አምስት መቶ ሺ. በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል።።

፫/ የዋጋ ቁጥጥር የሚደረግባቸውን የነዳጅ ውጤቶች መንግስት ከተመነው የመሸጫ ዋጋ በላይ ሲሸጥ የተገኘ የግብይት ተዋናይ በመጀመሪያ ጥፋት ከብር ሶስት መቶ ሀምሳ ሺ. እስከ አምስት መቶ ሺ. ይቀጣል፣ድርጊቱን በተደጋጋሚ ከፈጸመ ከሶስት አመት እስከ አምስት

he is aggrieved by the decision of the Ministry.

25 Criminal Penalty

1/ Any person who has been found storing or selling petroleum products out of the permitted place, person or marketing system or in containers specified by Directives to cause danger shall, in addition to the confiscation of such products, be punished with regorious imprisonment of three years to five years and with fine from Birr three handred fifty thousand to five hundred thousand.

2/Any person who intentionally Adulterates petroleum products and delivers them for marketing shall be punished with rigorous imprisonment from five years to seven years and with fine from Birr three hundred fifty thousand to five hundred thousand.

3/ Any market actor who is found selling price regulated petroleum products above the determined rate shall be punished for the first offense with fine from Birr three hundred fifty thousand to five hundred thousand, and if he commits it repeatedly, he

CamScanner

Made with Xodo PDF Reader and Editor

ዓመት እስራት እና ከብር ሦስት መቶ ሀምሳ ሺ. እስከ አምስት መቶ ሺ. ይቀጣል።

፬/ በሚመለከተው አካል የነዳጅ መቅጃ መሳሪያዎች የልኬት ሚትር ማስተካከያ ተደርጎበት በፕሎምቡ የታሰረውን የቀረጠ ወይም ልኬቱን ያዛባ ማንኛውም ሰው ከሦስት አመት እስከ ሰባት አመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት እና ከብር ሶስት መቶ ሀምሳ ሺ. እስከ አምስት መቶ ሺ. በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል።

፭/ የካሊብሬሽን የምስክር ወረቀት ሳይዝ ወይም ካልብሬት የተደረገውን የነዳጅ ውጤቶች ልኬት በማዛባት የነዳጅ ውጤቶችን ሲያጓጉዝ ወይም ሲሸጥ የተገኘ ማንኛውም ሰው የነዳጅ ውጤቶች ተወርሰው ከሦስት አመት እስከ ሰባት አመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት እና ከብር ሶስት መቶ ሀምሳ ሺ. እስከ አምስት መቶ ሺ. በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል።

፮/ የተረከባቸውን የነዳጅ ውጤቶች ከተፈቀደለት የማጓጓዣ መስመር ውጪ ሲያጓጉዝ፣ ከተፈቀደለት ማራገፊያ ውጪ ሲያራግፍ ወይም ወደ ጎረቤት ሀገር በኮንትሮባንድ ሲያጓጉዝ የተገኘ

shall be punished with simple imprisonment not exceeding three years and with fine from Birr one hundred thousand to five hundred thousand.

4/ Any person who detached a plumb seal or distorted calibrated meter of petroleum products shall be punished with rigorous imprisonment from three years to seven years and with fine from Birr three hundred fifty thousand to five hundred thousand.

5/ Any person who has been found transporting or selling petroleum products without a calibration certificate or distorting the calibrated equipment shall, in addition to the confiscation of petroleum products, be punished with rigorous imprisonment from three years to seven years and with fine from Birr three hundred fifty thousand to three hundred thousand.

6/ A carrier who has been found transporting or unloading petroleum products outside the permitted route or facility or smuggling to a neighboring country shall, in addition to the confiscation of such

CamScanner

Made with Xodo PDF Reader and Editor

ማንኛውም ሰው የተያዙት የነዳጅ ውጤቶች ተወርሰው ከአምስት አመት እስከ አስር አመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት እና ከብር አራት ሙቶ ሺ እስከ ሰባት ሙቶ ሺ በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል።

፯/ አግባብ ካለው አካል በጽሁፍ ፈቃድ ሳያገኝ የነዳጅ ውጤቶችን የነዳጅ ማደያ በሌለባቸው አካባቢዎች ሲሸጥ የተገኘ ማንኛውም ሰው የተያዘው የነዳጅ ውጤት ተወርሶ እስከ አምስት አመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከብር ሶስት ሙቶ ሺ እስከ አምስት ሙቶ ሺ በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል።

7/ Any person who has been found selling petroleum products in areas where there is no fuel station without obtaining the written permission of the Relevant Body shall, in addition to the confiscation of such products, be punished with regorious imprisonment not exceeding five years and with fine from Birr three hundred thousand to fifty hundred thousand.

፰/ የባለሥልጣኑን ወይም አግባብ ያለውን አካል የቁጥጥር ሂደት የተቃወመ፣ ያሰናከለ ወይም በማንኛውም ሁኔታ ተፅኖ ያደረሰ ማንኛውም ሰው ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከብር ሁለት ሙቶ ሺ እስከ አምስት ሙቶ ሺ በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል።

8/Any person who opposes, obstructs or unduly influences the controlling process of the Authority or the relevant Body shall be punished with simple imprisonment not exceeding three years and with fine from Birr two hundred thousand to five hundred thousand.

፱/ በዚህ አንቀጽ የተመለከቱት ድርጊቶች የሕግ ሰውነት ባለው አካል የተፈጸመ በሆነ ጊዜ ከብር ስድስት ሙቶ ሺ እስከ አንድ ሚሊዮን በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል።

9/ A juridical person who violates the provisions of this Article shall be fined from Birr six hundred thousand to one Million.

CamScanner

Made with Xodo PDF Reader and Editor

፲/ የነዳጅ ግብይት የዲጂታል ስርዓት ግዴታን የጣሰ፣ያጭበረበረ፣ተግባራዊ ያላደረገ፣የግብይት ተዋናይ ከሁለት አመት በማይበለጥ እስራት እና እስከ ብር ሶስት መቶ ሺ በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል።

10/ A juridical person who violates the provisions of this Article shall be fined from Birr Seven hundred thousand to one Million.

፲፩/በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪)፣ (፬)፣ (፭) ወይም (፮) የተመለከቱትን ድርጊቶች ለሁለተኛ ጊዜ በመፈጸም ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ የግብይት ተዋናይ በዚህ አንቀጽ ከሚጣልበት ቅጣት በተጨማሪ ድርጅቱ ለአምስት ዓመት እንዲዘጋ ይደረጋል።

11/ In addition to the penalty imposed by this article, a business actor who is found guilty of committing the actions referred to in sub Article (2), (4), (5) or (6) of this article for the second time his organization will be shut down for five years.

፲፪/በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚጣል የወንጀል ቅጣት በአስተዳደር የሚወሰድ እርምጃን አያስቀርም።

12/ Any person who obstructs the official's regulatory work by accepting bribes or commits a criminal offense shall be punished with rigorous imprisonment not exceeding five years and with fine from Birr two hundred thousand to five hundred thousand.

፳፮. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ይህን አዋጅ እና በአዋጁ መሠረት የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን በማስፈጸም ረገድ ማንኛውም ሰው ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት።

26. <u>Duty to Cooperate</u>

Any person shall have the duty to cooperate for the enforcement of this Proclamation, Regulations and Directives issued in accordance with this Proclamation.

CamScanner

Made with Xodo PDF Reader and Editor

ሸ፯. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ማንኛውም ነባር የግብይት ተዋናይ ይህ አዋጅ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ፮ (ስድስት) ወራት ጊዜ ውስጥ ለባለሥልጣኑ ማመልከቻ በማቅረብ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት።

ሸ፰.ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል።

፪/ ሚኒስቴሩ ይህንን አዋጅ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

ሸ፱.የተሻሩና ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጎች

፩/ የነዳጅና የነዳጅ ውጤቶች አቅርቦት ሥራ መቆጣጠሪያ አዋጅ ቁጥር ፰፻፴፰/፪ሺ፮ በዚህ አዋጅ ተሽሯል።

፪/ ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

27. **Transitional Provisions**

Any existing market actor shall apply to the Authority and obtain a Certificate of Competence within 6 (six) months from the effective date of this Proclamation.

28. **Power to Issue Regulations and Directives**

1/The Council of Ministers may issue Regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

2/The Ministry may issue Directives necessary for the implementation of this Proclamation and Regulations issued pursuant to sub-article (1) of this Article.

29. **Repealed and Inapplicable Laws**

1/Petroleum and Petroleum Products Supply Operation Proclamation No. 838/2014 is hereby repealed.

2/ No law or customary practices shall, in so far as they are inconsistent with the provisions of this Proclamation, have effect on matters provided under this Proclamation.

CamScanner

Made with Xodo PDF Reader and Editor

፴. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ የካቲት ፳፬ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም

ታዬ አጽቀሥላሴ
የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

30. Effective Date

This Proclamation shall enter into force upon the date of its publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 3rd day of March 2025.

TAYE ASTKE-SELLASIE
PRESIDENT OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF
ETHIOPIA

CamScanner